በአልቢኖ (ሻሾ)ልጆች ዙሪያ ጥያቄዎች እና መልሶች

በኤቨሪ ቻልድ ሚኒስትሪስ (ሁሉም ህጻናት አገልግሎት) የተዘጋጀ

ለተረሱ የአፍሪካ ህጻናትተስፋ የሚሰጥ ክርስቲያናዊ በጎ አድራጎት ድርጅት

ህፃናት የማንኛውም ሀገር ዋንኛ እሴት፥ ከእግዝአብሔር የተሰጡ ሀብት ናቸውና

አልቢኒዚም (ሻሾነት) ምንድን ነው?

አልቢኒዚም(ሻሾነት) ከዘር የተወረሰ ተፈጥሮ ነው። ይህ ተፈጥሮ ሜላኒን የተባለውን ለቆዳ፣ ለፀጉር እና ለአይን ቀለም የሚሰጥ ንጥረ ነገር እጥረት ሲያስከትል ፥ ቆዳና አይን የፀሃይ ብርሃን የመቋቋም አቅም አይኖራቸውም። የማየት ብቃታቸውም ደካማ ይሆናል።

አልቢኒዚም (ሻሾነት) በሽታ ነው?

አልቢኒዚም (ሻሾነት)በሽታ አይደለም። በበሽታ አምጪ ተዋህሲያን ወይም በቫይረስ ምክንያት አይደለም የሚመጣዉ። ይህ ተፈጥሮ ያለው ልጅ አልታመመም። አልቢኒዚም (ሻሾነት) እንደሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ልጁን አልያዘውም ወይም አልተጋባበትም። ወደ ሌሎች ሰዎችም በንክኪ ይህን ተፈጥሮ ሊያስተላልፍ አይችልም። አልቢኒዚም (ሻሾነት) ህመም (በሽታ) ስላልሆነ ይህ ተፈጥሮ ያለውን ሰው መንካት ምንም አይነት ጉዳት አያስከትልም።

በአልቢኖ (ሻሾ) ሰው የተዘጋጀ ምግብን ያለምንም ጉዳት መግዛት ወይም መመገብ ይቻላል?

ሙሉ በሙሉ አዎ። አልቢኖ (ሻሾ)ሰው አልታመም። በቀላሉ በዘር የሚመጣ ተፈጥሮ እንጂ ምንም አይነት በሽታ አምጪ ተዋህስያን ወይም ቫይረሶች ለአልቢኒዚም (ሻሾነት)መንስዔ አይደሉም።

አልቢኒዚም (ሻሾነት)እርግማን ነው?

እርግማን አይደለም። አልቢኒዚም (ሻሾነት)በዘር የሚተላለፍ ተፈጥሮ ነው። መጻህፍቅዱስ ሁሉም ልጆች ከእግዝአብሄር ዘንድ የተሰጡ በረከቶች እንደሆኑ ይናገራል። አልቢኖ (ሻሾ)የሆነ ልጅ እንደማንኛውም ልጅ ማደግ እና ለቤተሰቡ ለማህበረሰቡ እንዲሁም ለአለም በረከት መሆን ይችላል።

ነፍሰጡር ሴት የአልቢኖ (ሻሾ)ተፈጥሮ ያለውን ሰው ማየት በእርሷ ላይ እርግማን ያመጣል?

አያመጣም። ሌላ ሰውን መመልከት በሆድ ውስጥ ያለውን ፅንስ እድገት ሊቀይር (ሊጎዳ) አይችልም።

አልቢኖ (ሻሾ)የሆነ ልጅ መውለድ አሳፋሪ (ውርደት) ነው?

አይደለም። አልቢኖ (ሻሾ)ልጅ ከሌሎች በመልክ ይለያል፤ ነገር ግን የዚህ ልጅ መወለድ ለወላጆች ውርደት ሊሆን አይገባም። ልጅ ሁልጊዜም ቢሆን በረከት ነው።

አልቢኖ (ሻሾ)ሰዎች ልዩ በሽተኛን የመፈወስ ወይም ምትሃታዊ ችሎታ አላቸው?

የላቸውም። ልክ እንደሌሎቻችን ሁሉ እነሱም ሰው ናቸው። ከአልቢኖ (ሻሾ)ሰው ጋር የግብረ ስጋ ግኑኝነት ማድረግ ከምንም በሽታ አይፈውስም። የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸውም ቢሆኑም ምንም አይነት ልዩ ኃይል (ችሎታ)የላቸውም። አስማት (ጥንቆላን)የሚለማመዱ ሰዎች እነዚህን አይነት ውሸቶች ለማህበረሰቡ በመንገር እያታለሉ ገንዘብ ይሰበስባሉ። በፈረንጆች አቆጣጠር በ2007ዓ.ም በታንዛንያ ሀገር በእንደዚህ አይነት መልኩ ማህበረሰቡን በማታለል ብዙ አልቢኖ (ሻሾ)ሰዎች ለሞት ተዳርገዋል፤ ነገር ግን አንድም ህመምተኛ ሰው በዚህ መንገድ አልተፈወሰም። በዚምባቡዌ ሀገር አንድ አንድ ሰዎች ከአልቢኖ (ሻሾ)ሰዎች ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ ከኤድስ በሽታ ይፈውሳል ብለው ያምናሉ። ነገር ግን በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ ቅንጣት እንኳ ታህል እውነት የለበትም። አልቢኖ (ሻሾ)ሴቶች በእንደዚህ አይነት አስተሳሰብ ምክንያት ተገድደው ይደፈራሉ። ለኤድስ በሽታም ይጋለጣሉ።

አልቢኖ (ሻሾ)ሰዎች የአእምሮ ችግር አለባቸው?

አልቢኖ (ሻሾ)ሰዎች ምንም አይነት የአእምሮ ችግር የለባቸውም። እንደማንኛውም ሰው የማሰብ እና ማስተዋል ብቃት አላቸው። አልቢኖ (ሻሾ)ልጆች ዝግታ ሚታይባቸው ከሆነ ወላጆች በመጀመሪያ የልጆቻቸውን የማየት ችሎታ ማጣራት አለባቸው። የትምህርት ቤት ሰሌዳውን ለመመልከት እና ለማንበብ በድንብ ላይችሉ ይችላሉ። ይህም የመማር ሂደታቸውን ሊያቃውስ ይችላል። አንድ አንድ ጊዜ ጥቃቅን ፅሁፎችን መለየት ይቸገራሉ። በዚህም ምክንያት ማንበብ እና ሂሳብ ትምህርት ላይ ሊቸገሩ ይችላሉ። ነገር ግን የማየት ችሎታቸውን ለማሻሻል አስፈላጊው እርዳታ ከተደረገላቸው በእነዚህ እና በሌሎችም ትምህርቶች ጥሩ መስራት ይችላሉ።

ከላይ የተጠቀሱት ምክሮች የአልቢኖ (ሻሾ)ሰውን የማየት ችሎታ ካላሻሻሉ ሌላ ምን ማድረግ ይቻላል?

ይህ ሰው ወደ አይን ዶክተር በመሄድ መመር ይችላል። አንድ አንድ ግዜ የአይን መነፅር ሊረዳ ይችላል።ነገር ግን ማንኛውም አይነት መነፅር ሊሆን አይችልም። ለዛ ሰው አይን የተሰሩ መሆን አለባቸው። አንድ አንድ አልቢኖ (ሻሾ)ሰዎች በእጅ የሚያዝ ማጉያ መነፅር መጠቀም ይችላሉ። አንድ አንድ አልቢኒዚም (ሻሾነት)ተፈጥሮ ያላቸው ሰዎች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ማይት አይችሉም። እነዚህ ሰዎች ብሬል (የአይነ ስውራን ስርአተ ፅህፈት) መማር እና ህይወታቸውን እንደ ሌሎች ማየት የተሳናቸው ሰዎች መምራት ይችላሉ። ለአልቢኒዚም (ሻሾነት)ተፈጥሮ ያላቸው ሰዎች የፅህፈትን መጠን ማስተለቅ ብዙን ጊዜ

በተሻለ መንገድ እንዲያነቡ አይረዳቸውም። ይልቁንም ጽሁፍን በደማቅ ጥቁር እስክርቢቶ በንፁህ ነጭ ወረቅት ላይ ወይም በነጭ ጠመኔ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ማስፍር በይበልጥ ለማየት ይረዳቸዋል።

ለአልቢኖ (ሻሾ)ሰዎች የተለየ የአይን መነፅር ያስፈልጋቸዋል?

ተራ የአይን መነፅር ለአልቢኖ (ሻሾ)ሰዎች አይናቸው ከፀሀይ ጨረር እንዳይጎዳ ይከላከልላቸዋል። ምንም እንኳ የማየት ችሎታቸውን ባያሻሽልላቸውም አይንን ከደማቅ የፀሀይ ጨረር ሊደርስ ከሚችሉ ጉዳቶች ይጠብቃል። የአልቢኖ (ሻሾ)ሰው አይን ለፀሃይ ጨረር ከተጋለጠ ከፍተኛ የህመም ስሜትን ስለሚያስከትል የፀሀይ መከላከያ መነፅር ማድረግ ይህንን ለማስወገድ ይረዳል።

አልቢኖ (ሻሾ) ሰው ለስንት አመታት በህይወት ይኖራል?

የአልቢኒዚም (ሻሾነት)ተፈጥሮ ያላቸው ሰዎች ቆዳቸውን ለጎጂ የፀሃይ ብርሃን እስካላጋለጡ ድረስ ማንኛውም ሰው ሚኖረውን ያህል መኖር ይችላሉ። ኸርማንስኪ ፑድላክ ሲንድረም ከተባለ የአልቢኒዝም (ሻሾነት) አይነት ብቻ ጋር ሳምባን እና አንጀትን ሊጎዳ የሚችል የመድማት ችግር ተያይዞ ሊመጣ ይችላል። ይህም ደሞ እድሜን ሊቀንስ ይችላል። ነገር ግን ብዙ አልቢኖ (ሻሾ)ሰዎች ማንኛውም ሰው ሚኖረውን ያህል መኖር ይችላሉ። አልቢኒዝም (ሻሾነት)በእራሱ ሞትን ሊያስከትል አይችልም።

አልቢኖ (ሻሾ)ሰዎች አግብተው እና ልጅ ወልደው መኖር ይችላሉ?

አዎ የአልቢኒዝም ተፈጥሮ ያላቸው ሰዎች ልጅ መውለድ ፣ ቤት እና ቤተሰባቸውን መንከባከብ ይችላሉ። ሊያደርጉ ሚያስፈልጋቸው ብቸኛው ጥንቃቄ እራሳቸውን ከጎጂ የፀሃይ ጨረር መከላከል ነው።

የአልቢኖ (ሻሾ)ሰዎች የወደፊት ኑሮ ምን ሊመስል ይችላል?

አልቢኖ (ሻሾ)ሰዎች በህይወታቸው የተለያዩ ክፍሎች ላይ ስኬትን አስመዝግበዋል። አንድ የድሮ የጃፓን ሀገር ንጉስ ለምሳሌ የአልቢኒዝም(ሻሾነት)ተፈጥሮ ያለው ነበር። የቢዝነስ ሰዎች፣ መምህራን፣ አዳዲስ ልብሶችን ሚያስተዋውቁ ቆነጃጂት፣ ታዋቂ ተዋንያን፣ ኮመዲያን እና ሙዚቀኞች ሆነው የአልቢኒዝም(ሻሾነት)ተፈጥሮ ያላቸው ብዙ ሰዎች አሉ። የነዚህ ሰዎች ስኬት በግል ጥረታቸው እንዲሁም ከቤተሰብ እና ከማህበረሰብ በሚደረግላቸው ድጋፍ ላይ የተመሰረተ ነው። አልቢኖ (ሻሾ)ሰዎች በፀሃይ ጨረር ከሚደርስባቸው ጉዳት ለመከላከል ብዙ ውጭ መሆንን የማይጠይቅ ስራ ቢሰሩ ይመረጣል።

በይበልጥ ይህ ተፈጥሮ የሚኖራቸው ወንዶች ናቸው ወይስ ሴቶች ?

ሁለቱም በእኩል ደረጃ ይህ ተፈጥሮ ሊኖራቸው ይችላል።

አልቢኒዝም (ሻሾነት) በአፍሪካ ውስጥ ብቻ ነው ያለው?

አልቢኒዝም (ሻሾነት)በመላው አለም ላይ የሚገኝ ተፈጥሮ ነው። ነገር ግን በአፍሪካ ውስጥ በብዛት ያጋጥማል። እንዲሁም ጥቁር የቆዳ ቀለም ባላቸው ማህበረሰብ ውስጥ ይህ ተፈጥሮ በይበልጥ ጎልቶ ወጥቶ ይታያል። እንሰሳቶች እንኳ የአልቢኒዝም (ሻሾነት)ተፈጥሮ ሊኖራቸው ይችላል።

ወላጆች አንድ አልቢኖ (ሻሾ)ልጅ ከወለዱ ሌሎች የሚወልዷቸው ልጆች በሙሉ ይህ ተፈጥሮ ይኖራቸዋል ማለት ነው ?

ሊኖራቸውም ላይኖራቸውም ይችላል። አዲስ የሚወልዱት ልጅ አልቢኖ (ሻሾ)የመሆን አንድ አራተኛ እድል አለው።

እግዝአብሄር በእርግጥ ስለአልቢኖ (ሻሾ)ልጆች ግድ ይለዋል?

እግዝአብሄር ስለሁሉም ፍጥረት ግድ የለዋል። መጽሃፍ ቅዱስ ‘‘ሁለት ድንቢጦች በአምስት ሳንቲም ይሸጡ የለምን፤ ከእነርሱም አንዲቱ ያለ አባታችሁ ፈቃድ በምድር ላይ አትወድቅም’’ ይላል። እየሱስ የመስክ አበቦች እንኳ ሳይቀሩ በእርሱ እንክብካቤ ስር እንደሆኑ ተናግሯል [የማትዮስ ወንጌል 6: 26-27 (የማትዮስ ወንጌል ፮፥ ፳፮ እና፳፯) ]። እግዝአብሄር እያንዳንዱን ሰው ይወዳል። ‘‘በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና’’[ የዮሐንስ ወንጌል 3:16 (የዮሐንስ ወንጌል ፫ ፥፲፮) ]።

Every Child Ministries
P. O. Box 810
(875 S. State Road 2)
Hebron, IN 46341
ecmafrica@ecmafrica.org